


# العقيدة الصحيحة وما يضادها

# ትክክለኛ ዓቂዳ እና ተፃራሪው

(أمهري)

# ትክክለኛ ዐቂዳና ተጻራሪው

ቅንብር

ሸይኽ ዐብዱልዐዚዝ ብን ዐብደላህ ብን ባዝ

ተርጓሚ – ሙሐመድ ጀማል ሙክታር

**አሳታሚ**

በእስላማዊ ዳዕዋና ዕውቀት ማህበር
እስላማዊ ባህል ማዕከል
አዲስ አበባ ኅዳር 1986
አንደኛ እትም
ሁለተኛ እትም

بسم الله الرحمن الرحيم

# ትክክለኛ ዐቂዳና ተጻራሪው

ምሥጋና ለአላህ ይድረስ። ከአከብሮት የተቀናጀ እዝነትና ሰላም ለመጨረሻው ነቢይና ለቤተሰባቸው እንደዚሁም ለባልደረቦቻቸው (ለሰሓቦቻቸው) ይሁን።

ትክክለኛ ዐቂዳ (እምነት) የእስላም ሃይማኖት መሠረትና የእምነቱ የማዕዘን ድንጋይ እንደመሆኑ መጠን የገለጻዬ (ሌክቸሬ) ርዕስ አድርጌ መረጥኩ። በቁርአንና በነቢዩ (ሰዐወ)ሱንና ላይ ከተመረኮዙ ሸሪዓዊ ማስረጃዎች መረዳት እንደሚቻለው ሁሉ ማንኛውም አካላዊም ሆኑ አንደበታዊ ሥራዎች ትክክለኛ ሆነው መቆጠር የሚችሉትና ትክክለኛ ተደርገው የሚወሰዱት ከትክክለኛ ዐቂዳ(እምነት) ሲመነጩ ብቻ ነው። ያንድ ሰው ዐቂዳ (እምነት) ትክክለኛ ሆኖ ካልተገኘ በአካልም ሆነ በአንደበት የሚፈጽመው ማንኛውም ሃይማኖታዊ ሥራ ውድቅ ይሆናል። አላህ(ሱወ) እንዲህ ብሏልና:-

﴿ومن يكفر بالإيمان فقد حبط عمله
وهو في الآخرة من الخاسرين﴾.

*...ከእምነትም የሚመለስ ሰው በእርግጥ ሥራው ተበላሸ። በመጨረሻም ቀን እርሱ ከከሳሪዎቹ ነው።" 1*

﴿ولقد أوحي إليك وإلى الذين من قبلك لئن
أشركت ليحبطن عملك ولتكونن من الخاسرين﴾.

*በታጋራ ሥራህ በእርግጥ ይታበሳል፤ በእርግጥም ከከሓዲዎቹ ትኾናለህ ማለት ወደ አንተም ወደነዚያም ካንተ በፊት ወደ ነበሩት በእርግጥ ተወርዷል።"2*

---

1.አል-ማኢዳህ(5):5::

2.አል-ዙመር(39):65::

በዚህ ነጥብ ላይ አያሌ አንቀጾች ይገኛሉ። ግልጹ የአላህ መጽሐፍ ቁርአንና የታማኝ መልክተኛው (ሰዐወ) ሱንና (ፈለገ ሕይወት) ትክክለኛ ዐቂዳ በአላህ፣በመላዕክቱ፣ በመጻሕፍቱ፣በመልክተኞቹ፣በመጨረሻው ቀን(በትንሳኤ)ና መልካምም ሆነ መጥፎው በአላህ ዕውቀትና ውሳኔ የሚፈጸም መሆኑን በማመን የሚጠቃለል መሆኑን አመልክተዋል። እነዚህ ስድስት ነገሮች አሸናፊው የአላህ መጽሐፍ ይዟቸው የመጣና አላህ መልክተኛውን ሙሐመድን (ሰዐወ) የላከበት የትክክለኛ ዐቂዳ መሰረቶች ናቸው። ከሕዋሳት የራቁና ስለመኖራቸው እንድናምን ግዴታ የሆኑ ነገሮች ሁሉ አላህና ነቢዩ (ሰዐወ) የተናገሩዋቸው ጉዳዮች በሙሉ በነዚህ የእምነት መሠረቶች ሥር ይጠቃለላሉ። የነዚህ ስድስት መሠረቶች ማስረጃ በቁርአንና በሱና ውስጥ እጅግ ብዙ ናቸው። የሚከተለው የአላህ (ሱወ) ቃል ከነዚህ አንዱ ነው:-

﴿ليس البّر أن تولّوا وجوهكم قبل المشرق والمغـرب ولكن الـبّر من آمن بالله واليـوم الآخـر والملائكة والكتاب والنبيين﴾ الآية.

﴿آمن الـرسول بما أنزل إليه من ربه والمؤمنون كلٌ آمن بالله وملائكته وكتبه ورسله لا نفرّق بين أحد من رسله﴾ الآية.

*"መልካም ሥራ፣ ፊቶቻችሁን ወደ ምሥራቅና ምዕራብ አቅጣጫ ማዞር አይደለም: ግን መልካም ሥራ: በአላህና በመጨረሻው ቀን: በመላእክትም፣ በመጻሕፍትም፣ በነቢያትም ያመነ ሰው፣ ...ነው፤ ...."*3

---

3.አል-በቀራህ(2):177

﴿يا أيها الذين آمنوا آمِنوا بالله ورسوله
والكتاب الذي نزل على رسوله والكتاب الذي أنزل من قبل
ومن يكفر بالله وملائكته وكتبه ورسله واليوم الآخر فقد ضلّ
ضلالاً بعيدًا﴾.

﴿ألم تعلم أن الله يعلم ما في السماء
والأرض إن ذلك في كتاب إن ذلك على الله يسير﴾.

*መልክተኛው፣ ከጌታው ወደርሱ በተወረደው አመነ፤ ምእምኖቹም(እንደዚሁ) ፤ሁሉም በአላህ በመላእክቱም፣ በመጻሕፍቱም፣ በመልክተኞቹም፣ ከመልክተኞቹ በአንድም መካከል አንለይም፣(የሚሉ ሲኾኑ) አመኑ፤ . . .።"4*

*እላንተ ያመናችሁ ሆይ! በአላህና በመልክተኛው፣ በዚያም በመልክተኛው ላይ ባወረደው መጽሐፍ፣ በዚያም ከበፊቱ ባወረደው መጽሐፍ እመኑ፤ በአላህና በመላእክቱም፣ በመጽሐፎቹም፣ በመልክተኞቹም፣ በመጨረሻውም ቀን የካደ ሰው ፣(ከውነት) የራቀን መሳሳት በርግጥ ተሳሳተ።"5*

*አላህ በሰማይና በምድር ውስጥ ያለን ሁሉ በእርግጥ የሚያውቅ መኾኑን አታውቅምን? ይህ በመጽሐፍ ውስጥ (የተመዘገበ) ነው፤ ይህ በአላህ ላይ ገር ነው።"6*

---

4.አል-በቀራህ(2):285

5.አል-ኒሳእ(4):136

6.አል-ሐጅ(22):70

እነዚህን የእምነት መሠረቶች የሚመለከቱ ትክክለኛ ነቢያዊ ሐዲሶችም እጅግ ብዙ ናቸው። ከነዚህም መካከል መልአኩ ጅብሪል ስለ እምነት ነቢዩን ጠይቆ ነቢዩ የሰጡት መልስና በዑመር እብኑል ኸጧብ ተላልፎ በሙስሊም የተዘገበው የሚከተለው ታዋቂ ትክክለኛ ሐዲስ ይገኝበታል:-

الحـديث الصحيح المشهـور الـذي رواه مسلم في صحيحه من حديث أمير المؤمنين عمر بن الخطاب رضى الله عنه أن جبريل عليه السلام سأل النبي ﷺ عن الإيمان، فقال له: «الإيمان أن تؤمن بالله وملائكته وكتبه ورسله واليوم الآخر وتؤمن بالقـدر خيره وشره». الحـديث

*"እምነት (ኢማን) ማለት በአላህ በመላእክቱ በመጻሕፍቱ በመልክተኞቹ (በነቢዮቹ) ማመንና እንደዚሁም መልካሙም ሆነ መጥፎው በአላህ ዕውቀትና ፈቃድ የሚፈጸም መሆኑን ማመን ነው።"*[7]

አንድ ሙስሊም አላህን (ሱወ) አስመልክቶ ማመን የሚገባው፣ የትንሳኤውን ቀንና ሌሎች ከሕዋሳዊ ዕውቀት የራቁ ጉዳዮችን አስመልክቶ አምኖ መቀበል የሚገባው ማንኛውም ነገር በነዚህ በስድስቱ የእምነት መሠረቶች ውስጥ ይካተታሉ ወይም ከነሱ የሚመነጩ ናቸው።

አላህ(ሱወ) የፍጡራን ፈጣሪ: በጎ የሚውልላቸው፣ ሲሳይ የሚሰጣቸው፣ የደበቁትንም ሆነ የገለጹትን ሁሉ የሚያውቅና ለመልካም ሠሪው ምንዳ መስጠት አጥፊውንም መቅጣት የሚችል በመሆኑ አምልኮት ለርሱ ብቻ የተገባ እውነተኛው አምላክ መሆኑን ማመን በአላህ የማመን አካል ነው። ለዚህ አምልኮት ብሎም ነው አላህ(ሱወ) ሰውና አጋኔንትንም የፈጠራቸውና በዚህም ያዘዛቸው። ይህን አስመልክቶ እንዲህ ብሏል:-

---

7.ሙስሊም የዘገቡት ሐዲስ

﴿وما خلقت الجن والإنس إلاّ
ليعبدون ما أريد منهم من رزق وما أريد أن يطعمون إنّ الله
هو الرزاق ذو القوة المتين﴾.

*ጋኔንንና ሰውንም፣ ሊገዙኝ እንጂ ለሌላ አልፈጠርኳቸውም። ከነሱም ምንም ሲሳይን አልፈልግም፤ ሊመግቡኝም አልሻም። አላህ እርሱ ሲሳይን ሰጪ የብርቱ ኃይል ባለቤት ነው።"8*

﴿يا أيها الناس اعبدوا ربكم الذي خلقكم
والـذين من قبلكم لعلكم تتقون، الذي جعل لكم الأرض
فراشًـا والسـماء بنـاءً وأنـزل من السـماء ماءً فأخرج به من
الثمرات رزقًا لكم فلا تجعلوا لله أندادًا وأنتم تعلمون﴾.

*እላንተ ሰዎች ሆይ! የፈጠራችሁን፣ እነዚያንም ከናንተ በፊት የነበሩትን (የፈጠረውን) ጌታችሁን ተገዙ፤ (ቅጣትን) ልትጠነቀቁ ይከጀላልና።*

*"(እርሱ) ያ ለናንተ ምድርን ምንጣፍ፣ ሰማይንም ጣራ ያደረገ ነው፤ ከሰማይም (ከደመና) ውሃን ያወረደ፣ በርሱም ከፍሬዎች ለናንተ ሲሳይን ያወጣ ነው፤ እናንተም (ፈጣሪነቱን) የምታውቁ ስትኾኑ ለአላህ ባላንጣዎችን አታድርጉ።"9*

አላህ(ሱወ) ነቢያትን የላከውና መለኮታዊ መጻሕፍቱን ያስተላለፈው ይህን የአምልኮተ አላህ እውነታ ለማብራራትና ለዚሁ ጥሪ ለማድረግ ብሎ ነው። የዚህ ትክክለኛ ዐቂዳ ተጻራሪ ከሆነው ከባዕድ አምልኮ ያስጠነቀቀውም በዚህ ምክንያት ነው። አላህ(ሱወ) እንዲህ ብሏል:-

---

8.አል-ዛሪያት(51):56-58

9.አል-በቀራህ(2):21-22

﴿ولقد بعثنا في كل
أمّة رسولاً أن اعبدوا الله واجتنبوا الطاغوت﴾.

﴿وما أرسلنا من قبلك من رسول إلا نوحي
إليه أنّه لا إله إلا أنا فاعبدون﴾.

وقال عز وجلّ: ﴿كتاب أُحكمت آياته ثم فُصِّلت من لدن
حكيم خبير أن لا تعبدوا إلا الله إنني لكم منه نذير وبشير﴾.

*በየሕዝቡም ሁሉ ውስጥ፡ አላህን ተገዙ፤ ጣአትንም ራቁ፡ በማለት መልክተኛን በእርግጥ ልከናል፡. . . ።"10*

*ከአንተ በፊትም፡ እነሆ ከኔ ሌላ አምላክ የለምና ተገዙኝ፡ በማለት ወደርሱ የምናወርድለት ቢሆን እንጂ ከመልክተኛ አንድንም አልላክንም።"11*

*“. . .(ይህ ቁርአን) አንቀጾቹ በጥንክሬ የተሰካኩ፡ ከዚያም የተዘረዘሩ የኾነ መጽሐፍ ነው፤ ጥበበኛ ውስጠ አዋቂ ከሆነ ዘንድ (የተወረደ) ነው።*

የዚህ አምልኮ(ዕባዳ) እውነታ የሰው ልጅ በሚፈጽማቸው የመገዛት ተግባሮች ሁሉ በጸሎቱና በልመናው፡ በመፍራትና በመከጀልም፡ በሰላትና በጾምም፡ እርድ በማረድም ሆነ በስእለት፡ በተቀሩት የመግገዛት(የዕባዳ) ዓይነቶች ሁሉ ሀያሉን አላህ ብቻ በማሰብና ለርሱ ብቻ በማድረግ ለርሱ በመንበርከክ እርሱን በማፍቀርና ለሀያልነቱ በማጎብደድ በፍጹምነት ማከናወን ማለት ነው። አላህ (ሱወ) እንዲህ ብሏል:-

---

10.አል-ነሕል(16):36

11.አል-አንቢያ(21):25

أن لا تعبدوا إلا الله إنني لكم منه نذير وبشير﴾.

﴿فاعبد الله مخلصًا له الدين ألا لله الدين الخالص﴾.

﴿وقضى ربك أن لا تعبدوا إلا إياه﴾.

﴿فادعوا الله مخلصين له الدين ولو كره الكافرون﴾،

*" (እንዲህ በላቸው):- አላህን እንጂ ሌላን አትገዙ፤ እኔ ለናንተ ከርሱ (የተላከሁ) አስፈራሪና አብሳሪ ነኝ።"12*

*« . . . አላህንም ሃይማኖትን ለርሱ ብቻ ያጠራህ ኾነህ ተገዛው።"13*

*ጌታህም (እንዲህ ሲል) አዘዘ:- እርሱን እንጂ ሌላን አትገዙ፤. . ."14*

*አላህንም፣ ከሓዲዎች ቢጠሉም ሃይማኖትን ለርሱ አጥሪዎች ኾናችሁ ተገዙት።"15*

ቡኻሪና ሙስሊም ሙዓዝን ጠቅሰው በዘገቡት ሐዲስ መሠረት ነቢዩ(ሰዐወ) እንዲህ ብለዋል:-

وفي الصحيحين عن معاذ رضى الله عنه أن

النبي ﷺ قال: «حق الله على العباد أن يعبدوه ولا يشركوا به شيئًا».

*" አገልጋይ ፍጡራን ለአላህ ያለባቸው ግዴታ እርሱን ብቻ ማምለክና ምንም ነገር ከርሱ አለማጋራት (አለማሻረክ) ነው።"*

---

12.ሁድ(11):1-2

13.አል-ዙመር(39):2

14.አል-ኢስራእ(17):23

15.አል- ሙእሚን(40):14

አላህ በባሮቹ ላይ በደነገገባቸውና ግዴታ አድርጎ በወሰነባቸው እንደ አምስቱ ግልጽ የእስላም ማዕዘን ባሉት ነገሮች ሁሉ ማመንም በአላህ የማመን አካል ነው። ማዕዘኖቹም:- ከአላህ በስተቀር ሌላ አምላክ አለመኖሩንና ሙሐመድም የአላህ መልክተኛ መሆናቸው መመስከር: ሰላትን አዘውትሮ መስገድ: ዘካት መክፈል: የረመዳናንን ወር መጾምና አቅሙ ካለ የሐጅ ሥርዓት ጸሎት ወደ መካ ተጉዞ መፈጸም ናቸው። ከነዚህ ከአምስት ማዕዘኖች ዋነኛውና ትልቁ ከአላህ በስተቀር ሌላ አምላክ እንደሌለና ሙሐመድም መልክተኛው መሆናቸውን መመስከር ነው። ከአላህ በስተቀር ሌላ አምላክ የለም ብሎ መመስከር አምልኮትን በፍጹምነት ለአንድ አላህ ብቻ ማድረግንና ከርሱ በስተቀር አምልኮ(ዕባዳ) ለማንም የማይገባ መሆኑን በማረጋገጥ ባዕድ አምልኮን ከነጭራሹ ማስተባበልን ግዴታ ያደርጋል። የ ላኢላሃ ኢላሏህ" ትርጉምም የኸው ነው። ሊገገዙትና ሊያመልኩት የሚገባው እውነተኛ አምላክ አላህ ብቻ ነው። ከርሱ ሌላ የሚያመልኩት ሰውም ሆነ ወይም መልአክ ወይም አጋኔንት ወይም ሌላ ነገር ሁሉ የውሸት አምላክ ነው። እውነተኛውም አምላክ አላህ ብቻ ነውና። አላህ(ሱወ) እንዲህ ብሏል:-

﴿ذلك بأن الله هو الحق وأن ما يدعون من دونه هو الباطل﴾

*“ ይህ: አላህ እርሱ እውነት በመኾኑ: ከርሱም ሌላ የሚገገዙት ነገር እርሱ ፍጽም ውሸት በመኾኑ: . . ”16*

አላህ(ሱወ) ሰውንና አጋኔንትን ለዚህ የመገገዛት (ዕባዳ) ዓላማ የፈጠራቸውና ያዘዛቸው ስለመሆኑ: ነቢያትንም የላካቸውና መጻሕፍቱንም ያወረዳቸው ለዚሁ መሆኑን ከላይ አብራርተናል። ይህን ነጥብ በደንብ አስተውሉ: በሚገባም አስተንትናችሁ ተረዱት። ባዕድ አምልኮን አስመልክቶ ብዙ ሰዎች የወደቁበት ትልቅ ማይምነትና በዚህም ምክንያት ለአላህ የሚገቡ ነገሮች ለሌሎች እንዴት እንዳዛወሩ ግልጽ ይሆንላችኋልና።

---

16. አል-ሐጅ(22):62

አላህ የዓለማት ፈጣሪ፣ የፍጡራን ጉዳዮች ሁሉ አቀነባባሪ፣ በውቀቱና በችሎታው እንዳሻው የሚያዝባቸው አስፈጻሚ አምላክ መሆኑን ማመንም በአላህ የማመን አካል ነው። እርሱ የቅርቢቱ ዓለምና የወዲያኛው ዓለም ባለቤትና የዓለማት ሁሉ ጌታ ነው። ከርሱ በስተቀር ሌላ ፈጣሪ የለም። ከርሱ ወዲያ ሌላ ጌታ የለም። ለፍጡራን አገልጋዮቹ ጥቅምና መመሪት ብሎ በቅርቢቱም ሆነ በወዲያኛው ሕይወታቸው ድልና ተድላን መጎናጸፍ ወደሚያስችላቸው መመሪያ ሊጠራቸው ዘንድ ነቢያትን ልኳል። መለኮታዊ መጻሕፍቱንም አስተላልፎዋል። ይህን ሁሉ ሲያደርግ በዚህ ሁሉ ውስጥ ምንም ዓይነት አጋርና ሸሪክ የለውም። እንዲህ ብሏልና:-

﴿الله خالق كل شيء وهو على كل شيء وكيل﴾.

﴿إن ربكم الله الذي خلق السموات والأرض
في ستة أيام ثم استوى على العرش يغشي الليل النهار يطلبه
حثيثًا والشمس والقمر والنجوم مسخرات بأمره ألا له الخلق
والأمر تبارك الله رب العالمين﴾.

*"አላህ የነገሩ ሁሉ ፈጣሪ ነው። እርሱም በነገሩ ሁሉ ላይ አስተናባሪ ነው።"17*

*ጌታችሁ ያ ሰማያትንና ምድርን በስድስት ቀኖች ውስጥ የፈጠረ አላህ ነው፣ ከዚያም በዐርሹ ላይ (በዙፋኑ ላይ) ተደላደለ፣ (አላህ) ሌሊትን በቀን ፈጥኖ የሚፈልገው ሲሆን ይሸፍናል፣ ጸሐይንና ጨረቃንም፣ ከዋክብትንም በትእዛዙ የተገሩ ሲሆኑ(ፈጠራቸው)፣ ንቁ፣ መፍጠርና ማዘዝ የርሱ ብቻ ነው። የዓለማት ጌታ አላህ (ክብሩ) ላቀ።18*

---

17.አል-ዙመር(39):62

18.አል-አዕራፍ (7):54

አሸናፊ መጽሐፉ (ቁርአን) ውስጥ በተመለከቱትና በታማኝ መልክተኛው ሐዲስ በተረጋገጡት፣ የአላህ መልካም ስሞችና ሀያል ባህሪያቱ ምንም ሳያዛንፉና ትርጉም አልባ ባዶ ቃላት ሳያደርጉ፣ ከፍጡራን ባህሪያት ጋር ሳያመሳስሉና ሳያነጻጽሩ ማመንም በአላህ የማመን አንዱ ክፍል ነው። እነዚህ የአላህ ስሞችና ባህሪያት (አል አስማኡ ወስ- ሲፋት) አላህና ነቢዩ (ሰዐወ)በገለጹት መሰረት እንዲህ ናቸው እንደዚያ ናቸው ሳይባሉ እንዳሉ መቀበልና በሚያመለክቱት ታላላቅ ትርጉሞችና ይዘት ማመን ግዴታ ነው። በነዚህ ባህሪያት አላህን መግለጽ ማለት ለሀያልነቱ ተገቢ በሆነ መንገድ ከፍጡራን ጋር በምንም ሳያመሳስሉትና ሳያዛምዱ መግለጽ ማለት ነው። ይህን አስመልክቶ አላህ (ሱወ) እንዲህ ብሏልና:-

﴿ليس كمثله شيء وهو السميع البصير﴾.

وقال عز وجل: ﴿فلا تضربوا لله الأمثال إن الله يعلم وأنتم لا تعلمون﴾.

*« ...የሚመስለው ምንም ነገር የለም፤ እርሱም ሰሚው ተመልካቹ ነው።"19*

*"ለአላህም አምሳያዎችን አታድርጉ፤ አላህ(መሳይ እንደሌለው) ያውቃል፣ እናንተ ግን አታውቁም።"20*

---

19.አል-ሹራ(42):11

20.አል-ነሕል(16):74

ይህ ነው እንግዲህ ከአላህ መልክተኛ(ሰዐወ) ባልደረቦች(ሰሓባ) እና እነሱን በቅንነት ከተከተሉት ተከታዮች የተላለፈው የሱን'ና ሰዎች (አህሉ'ስሱና) ዐቂዳ። ኢማም አቡል ሐሰን አል አሸዐሪ አልመቃላት" በተባለ መጽሐፋቸው ውስጥ የሐዲስ ሊቃውንትንና የሱን'ና ሰዎችን በመጥቀስ ያስተላለፉት ዐቂዳም ይኸው ነው። ሌሎች የዕውቀትና የእምነት ባለቤቶችም ይህንኑ ነው ያስተላለፉት።

አል አውዛዒ የተባሉት ሊቅ በዘገቡት መሠረት አዝዙህሪና መክሑል የተባሉ ዓሊሞች የአላህን ባህሪያት (ሲፋት) ስለሚመለከቱ የቁርአን አንቀጾች ተጠይቀው: እንዳሉ ሳትተቹበት ተቀብላችሁ እመኑባቸው ብለዋል። ኢማም ማሊክ፣ አል አውዛዒ፣ለይስ ብን ሰዓድና ሱፍያን አስሰውሪ የአላህን ባህሪያት ስለሚመለከቱ ሐዲሶች ተጠይቀው እንዲህ ነው እንደዚያ ነው ሳትሉ እንዳሉ ተቀብላችሁ በማመን አሳልፉአቸው በማለት መመለሳቸውን ወሊድ ብን ሙስሊም ዘግበዋል። እኛና ቁጥራቸው በርከት ያለ ታቢዕዮች (ከሰሓባ ለጥቆ የነበረው ሁለተኛው የእስላም ትውልድ) አላህ ከዐርሹ(ከዙፋኑ) በላይ መሆኑን እንናገር ነበር። ባህሪያትን (ሲፋትን) አስታክኮ ነቢዩ(ሰዐወ) ሱን'ና ውስጥ በተመለከቱት ጉዳዮች ሁሉ እናምን ነበር በማለት አል አውዛዒ ተናግረዋል። የኢማም ማሊክ አስተማሪ የነበሩት ረቢዓ ብን አቢ ዐብዱረህማን ስለ መደላደል (እስትዋእ) ሲጠየቁ:- መደላደል(እስትዋእ) የማይታወቅ ነገር አይደለም። መልዕክቱ ከአላህ የተላለፈ ነው። የመልክተኛው(የነቢዩ) ግዴታም የታዘዙትን በግልጽ ማድረስ ብቻ ነው። የኛ ፈንታ ደግሞ አምኖ መቀበል ነው።" በማለት መልሰዋል። ኢማም ማሊክም ስለዚሁ ጉዳይ ሲጠየቁ እንዲህ ብለዋል:-

«الاستواء معلوم والكيف مجهول والإيمان به واجب والسؤال عنه بدعة»

*መደላደል (እስትዋእ) ግልጽ ጉዳይ ነው። አኳኋኑ (ሁኔታው) የማይታወቅ ነው። በርሱ ማመኑ ግዴታ ዋጂብ ነው። ስለዚህ ጉዳይ አንስቶ ጥያቄ ማቅረብ ደግሞ ብድዓ (በሃይማኖቱ ላይ ከራስ ስሜት አዲስ ፈጠራ መጨመር) ነው።"*

ከዚያም ኢማሙ ለጠያቂው ሰው መጥፎ ሰው እንደሆንክ ነው የሚታየኝ አሉትና እንዲወጣ አዘው እንዲወጣ ተደረገ። የዚሁ ይዘት ያለው አቋም ከእሙ-ምዕመናን ኡምሙ ሰላማ ተላልፎአል። ኢማም አቡ ዐብዱረማህ ዐብደላህ ብን ሙባረክ:- ጌታችን (ሱወ) ከሰማያቱ በላይ ከፍጡራን ፍጹም በተለየ ሁኔታ ከዙፋን(ዐርሹ) በላይ መሆኑን እናውቃለን።" ማለታቸው ተዘግቦአል። የእስላም መሪ ሊቃውንትም በዚህ ነጥብ ላይ ያስተላለፉት ብዙ ስለሆነ በዚህ ገለጣ ጠቅሶ ማዳረስ አመቺ አይደለም። በዚህ ጉዳይ ላይ የበለጠ ማብራሪያ የሚፈልግ ሰው የሱና ሊቃውንት በርዕሱ ላይ የጻፉትን ለምሳሌ የኢማም አህመድ ልጅ የዐብዱላህ "ሱን'ና" መጽሐፍን የኢማም ሙሐመድ ብን ኹዘይማን "አትተውሒድ" መጽሐፍን፣ የአቡል ቃሲም አልላካኢ"ሱን'ና" መጽሐፍን፣ የአቡበክር ብን ዓሲምን"ሱን'ና" መጽሐፍንና ሸይኹል እስላም እብኑ ተይምያህ ለሐማ ሰዎች የሰጡትን ምላሽ ማንበብ አለባቸው። የእብኑ ተይምያህ ምላሽ ትልቅ ቁም ነገር ያለው ሲሆን የአህሉ-ሱን'ናን ዐቂዳ ያብራሩበትና ሸሪዓዊና ሕሊናዊ ማስረጃዎችን ያስተላለፉበት ጠቃሚ ምላሽ ነው። የአህለ-ሱንና አቋም ትክክለኛነትና የተቃራኒዎቻቸውን ስሕተት በግልጽ አስቀምጠውበታል። "አትተይመሪያ" በሚል ርዕስ ባቀረቡት ጽሑፋቸው ውስጥም እንደዚሁ የአህሉ-ሱንና ዐቂዳ በሸሪዓዊና ሕሊናዊ ማስረጃዎች ያረጋገጡበት ተቃራኒ አቋም ላላቸው ወገኖች ሐቅን ግልጽ በሚያደርግና ውሸትን በሚያስወግድ ሁኔታ ማብራሪያ የሰጡበት ጽሑፍ ነው። ጽሑፉ በቅን አሳቢነትና እውነትን ለማወቅ ካለው ፍላጎት ተነስቶ ለተመለከተ የዕውቀት ሰው ሁሉ ሐቅን የሚያስጨብጥ ጽሑፍ ነው። የአላህን ስሞችና ባህሪያት (አል አስማእ ወስ-ሲፋት) አስመልክቶ የሱን'ና ሰዎች የሚያምኑበትን ዐቂዳ የሚቃረን ሰው ሸሪዓዊና ሕሊናዊ ማስረጃዎችን የመጻረር ስህተት ላይ ከመውደቁም ባሻገር በሚያረጋግጠውና በሚያስተባብለው ነገር ሁሉ ውስጥ ግልጽ የሆነ መፋለስ ያጋጥመዋል።

የአህሉ-ሱን'ና ወገኖች አላህ(ሱወ) በመጽሐፉ ውስጥ ወይም መልክተኛው ሙሐመድ(ሰዐወ) በትክክለኛ ሐዲሳቸው ውስጥ ስለ አላህ መልካም ስሞችና ታላላቅ ባህርያት ያረጋገጡትን ሁሉ ከፍጡራን ጋር ምንም ዓይነት ማመሳሰልና ንጽጽሮሽ በማይቀበል ሁኔታ

ያረጋግጡለታል። አላህን ከፍጡራን ባህርያትና ከማንኛውም ምሳሌ ያጠሩታል። የላቁ ባህርያቱን ትርጉም የለሽ ባዶ ቃል ከማድረግ ነጻ በሆነ ሁኔታ ተቀብለው ይገልጹታል። በዚህ አቋማቸውም እርስ በርሱ ከሚቃረን የተፋለሰ አቋም ድነው ሁሉንም ማስረጃዎች ለመተግበር በቅተዋል። ይህም አላህ(ሱወ) መልክተኞቹን የላከበትን እውነታ በመያዝ የተቻለውን ጥረት ላደረገ በፍጹምነት ሐቅን በመፈለጉ አላህ እውነትን ለማግኘት ላደለውና ማስረጃዎቹን ለአሸናፊነት ላበቃለት ወገን የአላህ(ሱወ) ሕግ ነው። አላህ(ሱወ) እንዲህ ብሏልና:-

﴿بل نقذف بالحق على الباطل فيدمغه فإذا هو زاهق﴾.

﴿ولا يأتونك بمثل إلاّ جئناك بالحق وأحسن تفسيراً﴾.

*በእርግጥ እውነትን በውሸት ላይ እንጥላለን: አንጎሉን ያፈርሰዋልም: ወዲያውም እርሱ ጠፊ ነው: . . . "21*

*በጥያቄም አይመጡብህም: እውነተኛውን (መልስ): መልካም ፍችም የምናመጣልህ ብንኾን እንጂ።"22*

እብኑ ከሲር በታዋቂው የቁርአን ትንታኔ መጽሐፋቸው ውስጥ ቀጥሎ የቷመለከተውን የቁርአን አንቀጽ ሲተነትኑ መልካም ቃላት አስፍረዋል።

---

21. አል - አንቢያ (21):18

22. አል- ፉርቃን (25):33

﴿إن ربكم الله الذي خلق
السموات والأرض في ستة أيام ثم استوى على العرش﴾

*"ጌታችሁ ያ ሰማያትና ምድርን በስድስት ቀኖች ውስጥ የፈጠረ አላህ ነው፣ ከዚያም በዐርሹ ላይ (በዙፋኑ ላይ) ተደላደለ:. . ."23*

እብኑ ከሲር ይህን አንቀጽ አስመልክተው የጻፉት ነገር በዚህ ጉዳይ ላይ ትልቅ ጠቀሜታ ያለው በመሆኑ እዚህ ላይ መጥቀሱ ጥሩ ይሆናል:-

በዚህ ቦታ ላይ ሰዎች በጣም ብዙ አባባሎች አሏቸው። እዚህ መዘርዘር የማያመቹ። እኛ በዚህ ጉዳይ ላይ የምንከተለው መንገድ የደጋግ አበውን(አስ-ሰለፉ-ሷሊህ) የነ ማሊክን አውዛዒን፣ ሰውሪን፣ ለይስ ብን ሰዕድን፣ የነሻፊዒን፣ አሕመድን እስሐቅ ብን ራህዌህንና የሌሎቹን የጥንትና የቅርብ ዘመን የእስላም ሊቃውንት መንገድ ነው። ይህም መንገድ እንዲህ ነው እንደዚያ ነው ሳይሉ ከፍጡራን ባህርያት ጋር ሳያመሳስሉና ሳያነጻጽሩ፣ ትርጉም አልባ ባዶ ቃልትም ሳያደርጉ እንዳሉ ተቀብለው በማመን ያለሀተታ ማሳለፍ ነው። ከፍጡራን ጋር የማመሳሰል ግንዛቤ ቶሎ ወደ አእምሮአቸው የሚመጣባቸው ሰዎች አላህ(ሱወ) ከሚያስቡት ሁሉ ፍጹም የጠራ መሆኑን፣ እርሱን የሚመስል ምንም ነገር አለመኖሩን፣ እርሱ ምንም አምሳያ የሌለው ሰሚ ተመልካች መሆኑን መረዳት ይኖርባቸዋል። ትክክለኛው አቋም ነዒም ብን ሐማድ አል ኹዛዒ የቡኻሪ አስተማሪ(ሸይኽ) እና ሌሎችም ኢማሞች እንዳሉት ሁሉ:-

---

23.አል-አዕራፍ(7):54

አላህን ከፍጡራት ጋር ያመሳሰለና ያነጻጸረ ሰው ከሓዲ (ካፊር) ነው። አላህ ራሱን ከገለጸባቸው ወይም መልክተኛው ከገለጹት ባህሪያቱ መካከልም ምንም ዓይነት የማነፃፀርና የማመሳሰል(ተሽቡህ) ሁኔታ የለም። ቀጥተኛ ትርጉም ባላቸው የቁርአን አንቀጾችና በትክክለኛው የነቢዩ(ሰዐወ) ሐዲስ የተመለከቱትን የአላህ ስሞችና ባሕርያት ለኃያልነቱ በሚገባ መንገድ ያረጋገጠና ከጎዶሎ የፍጡራን ባህሪያት ሁሉ አላህን ያጠራ ሰው ቀጥተኛውን ጎዳና ተከትሏል።

በመላእክት(መላእካህ) ማመንም ጠቅለል ያሉና የተዘረዘሩ ጉዳዮችን ያካትታል። አንድ ሙስሊም፣ አላህ እንዲታዘዙት የፈጠራቸውና የተከበሩ ባሮች መሆናቸውን የገለጸ ከትዕዛዙ የማይወጡ ቅን ታዛዥ የሆኑ መላእክት እንዳሉት ያምናል። አላህ (ሱወ) ይህንኑ በማስመልከት ቁርአን ውስጥ እንዲህ ብሏል:-

﴿يعلم ما بين أيديهم وما خلفهم ولا يشفعون إلاّ لمن ارتضى وهم من خشيته مشفقون﴾.

*...(መላእክት) የተከበሩ ባሮቹ ናቸው። በንግግር አይቀድሙትም: (ያላለውን አይሉም): እነሱም በትእዛዙ ይሰራሉ። በፊታቸው ያለውንና በኋላቸው ያለውንም ሁሉ ያውቃል: ለወደደውም ሰው እንጅ ለሌላው አያማልዱም: እነሱም እርሱን ከመፍራታቸው የተነሳ ተጨናቂዎች ናቸው"24*

24.አል-አንቢያ(25):26-28

መላእክት በብዙ ይፈረጃሉ። ከመካከላቸው የአላህን ዐርሽ (ዙፋን) ለመሸከም የተመደቡ: በገነትና በገሐነም ላይ የተመደቡና የሰው ልጆችን ሥራዎች ለመመዝገብ የተመደቡ ቡድኖች ይገኛሉ። በዝርዝር ልናምንባቸው የሚገቡት አላህና መልክተኛው በስም የጠቀሷቸውን እንደ ጅብሪል(ገብሬል): ሚካኤል: የገሐነም እሳት ኃላፊ ማሊክና በመለከቱ ነፊ የሆነው እስራፊል በመሳሰሉት ነው። በትክክለኛ የነቢዩ(ሰዐወ) ሐዲስ ተመልክተዋልና። መላእኮች ከምን እንደተፈጠሩ በማስመልከት ነቢዩ(ሰዐወ) የተናገሩት ትክክለኛ ሐዲስ በኢመ-ምእመናን አዕሻ አማካይነት እንደሚከተለው ተዘግቧል:-

«خلقت الملائكة من نور وخلق الجان من مارج من نار وخلق آدم مما وصف لكم» أخرجه مسلم في صحيحه .

*" መላእኮች ከብርሃን ተፈጠሩ: አጋኜንት ደግሞ ጢስ ከሌለው እሳት ተፈጠሩ: አደም ደግሞ ከተገለጸላችሁ ነገር (ከአፈር) ተፈጠረ።"25*

በመለኮታዊ መጻሕፍት ማመንም እንደዚሁ ጠቅለል ባለ መልኩ አላህ(ሱወ) ሰዎችን ወደ አምልኮተ አላህ ይጠሩ ዘንድ ወደ መረጣቸው ነቢያትና መልክተኞቹ መሪ መጻሕፍት ያስተላለፈ መሆኑን ማመን ነው። አላህ(ሱወ) እንዲህ ብሏል:-

﴿لقد أرسلنا رسلنا بالبيّنات وأنـزلنا معهم الكتاب والميزان ليقوم الناس بالقسط﴾ الآية .

*"መልክተኞቻችንን በግልጽ ማስረጃዎች በእርግጥ ላክን: ሰዎችም በትክክል ቀጥ እንዲሉ: መጽሐፎችንና ሚዛንን ወደነርሱ አወረድን: . . ."26*

---

25.ሙስሊም የዘገቡት ሐዲስ

26.አል-ሐዲድ(57):25

﴿كان الناس أمّة واحدة فبعث الله النبيين مبشرين ومنذرين وأنـزل معهم الكتاب بالحق ليحكم بين الناس فيما اختلفوا فيه﴾ الآية.

*ሰዎች ሁሉ አንድ ሕዝብ ነበሩ፤ (ተለያዩ)፤ አላህም ነቢያትን አብሳሪዎችና አስፈራሪዎች አድርጎ ላከ፤ ከነርሱም ጋር መጻሕፍትን በሰዎች መካከል በዚያ በርሱ በተለያዩበት ነገር ይፈርድ ዘንድ በእውነት አወረደ:. . . "27*

ከመለኮታዊ መጻሕፍቱ መካከል አላህ በስም ለይቶ በጠራቸው እንደ ተውራት(ኦሪት)፣ እንጂል(ወንጌል)፣ ዘቡር(መዝሙረ ዳዊት) እና ቁርአን ባሉት ዝርዝር ባለ መልኩ እናምንባቸዋለን። ቁርአን ከሁሉም በላጩና የሁሉም መደምደሚያ ነው። በሁሉም ላይ ተቆጣጣሪና አረጋጋጭ ነው። ሕዝቦች በመላ ሊከተሉትና ሊዳኙበት የሚገባ መጽሐፍ ነው። አላህ(ሱወ) መልክተኛው ሙሐመድን (ሰዐወ) ለመላው የሰው ዘርና ለአጋኔንም መልክተኛ አድርጎ ልኳቸዋል። በመላው የሰው ዘር መካከል በርሱ ይፈርዱ ዘንድ ይህን ቁርአን ለልብ ጥመት ፈውስ፣ሁሉንም ነገር የሚያብራራ ለምዕመናን መመሪያና ርህራሄ አድርጎት ወደ ነቢዩ(ሰዐወ) አስተላልፎታል። ይህንኑ አስመልክቶ አላህ(ሱወ) እንዲህ ብሏል።

﴿وهذا كتاب أنزلناه مبارك فاتبعوه واتقوا لعلكم ترحمون﴾.

---

27. አል-በቀራህ(2):213

﴿ونزّلنا عليك الكتاب تبيانًا لكل شيء وهدى ورحمة وبشرى للمسلمين﴾.

﴿قل يا أيها الناس إني رسول الله إليكم جميعًا الذي له ملك السموات والأرض لا إله إلاّ هو يحيي ويميت فآمنوا بالله ورسوله النبي الأمي الذي يؤمن بالله وكلماته واتبعوه لعلكم تهتدون﴾.

*"ይህም ያወረድነው የኾነ የተባረከ መጽሐፍ ነው፤ ተከተሉትም፤ ይታዘንላችሁም ዘንድ (ከክሕደት) ተጠንቀቁ።"28*

*"...መጽሐፉንም ለሁሉም ነገር አብራሪ፣ መሪም እዝነትም፣ ለሙስሊሞችም አብሳሪ ኾኖ ባንተ ላይ አወረድነው።"29*

*"(ሙሐመድ ሆይ!) በላቸው እላንተ ሰዎች ሆይ! እኔ ወደናንተ ወደሁላችሁም የአላህ መልክተኛ ነኝ፤ (እርሱም) ያ የሰማያትና የምድር ንግሥና ለርሱ ብቻ የኾነ ነው፤ እርሱ እንጂ ሌላ አምላክ የለም፤ሕያው ያደርጋል፤ ይገድላልም፤ በአላህ፣ በአላህና በቃላቶቹ የሚያምነው የማይጽፍ የማያነብ ነቢይ በሆነው መልክተኛው እመኑ፤ ቅኑንም መንገድ ትመሩ ዘንድ ተከተሉት።"30*

አላህ በላካቸው ነቢያትና መልክተኞችም እንደዚሁ በጥቅሉና ዘርዘር ባለ ሁኔታ ማመን ግዴታ ይሆናል። ስለዚህም አላህ(ሱወ) ወደ ሰው ልጆች ከመካከላቸው መርጦ አብሳሪና አስጠንቃቂ ሆነው ወደ እውነት እንዲጠሩዋቸው መልክተኞችን የላከ መሆኑን እናምናለን።

---

28.አል-አንዓም(6):155

29.አል-ነሕል(16):89

30.አል-አዕራፍ(7):158

ለመልክተኞቹ ጥሪ አወንታዊ ምላሽ የሰጠ ሰው ተድላን ይጎናጸፋል። መልክተኞቹን የተጻረራቸው ሰው ደግሞ ውድቀትና ጸጸት ይገጥመዋል። የመልክተኞቹ መደምደሚያ ከሁሉም በላጩ ነቢያችን ሙሐመድ ብን ዐብደላህ(ሰዐወ) ናቸው። አላህ(ሱወ) እንዲህ ብሏል:-

﴿ولقد بعثنا في كل أمة رسولاً أن اعبدوا الله واجتنبوا الطاغوت﴾.

وقال تعالى: ﴿رسلاً مبشرين ومنذرين لئلّا يكون للناس على الله حجة بعد الرسل﴾.

وقال تعالى: ﴿ما كان محمد أبا أحد من رجالكم ولكن رسول الله وخاتم النبيين﴾.

*በየሕዝቡም ሁሉ ውስጥ: አላህን ተገዙ: ጣዖትንም ራቁ በማለት መልክተኛን በእርግጥ ልከናል: . . . "31*

*ከመልክተኞቹ በኋላ ለሰዎች በአላህ ላይ አስረጅ እንዳይኖር አብሳሪዎችና አስፈራሪዎች የኾኑን መልክተኞች (ላክን): . . . "32*

*ሙሐመድ: ከወንዶቻችሁ የአንድም ሰው አባት አይደለም: ግን የአላህ መልክተኛና የነቢዮች መደምደሚያ ነው: . . . "33*

ከመልክተኞቹ ውስጥ አላህ በስም ለይቶ የጠቀሳቸውን ወይም የአላህ መልክተኛ (ሰዐወ) በስም የጠቀሷቸው መሆናቸው ከተረጋገጠ እንደ ኑሕ: ሁድ: ሷሊህ: ኢብራሂምና ሌሎችንም ለይተን እናምንባቸዋለን።

---

31.አል-ነሕል(16):36

32.አል-ኒሳእ(4):165

33.አል-አሕዛብ(33):40

በመጨረሻው ቀን ማመን ደግሞ አላህና ነቢዩ(ሰዐወ) የተናገሩትን ከሞት በኋላ እንዳሉት የመቃብር ውስጥ ሥቃይን: ጭንቅና ደስታውን በመሳሰሉ ጉዳዮች ማመንን: በትንሳኤ ቀን በሚከሰቱ አስፈሪ ክስተቶችና አስበርጋጊ ትዕይንቶች: በሲራጥ(ገሐነም ላይ የተዘረጋ ከፀጉር የቀጠነ ከሰይፍ የሰላ ድልድይ): በሥራዎች መመዘንና በምርመራ ማመንን: እንደዚሁም ሁሉም እንደ የሥራው ተገቢ ዋጋውን የሚያገኝ መሆኑን: ሥራዎች የተመዘገቡባቸው ፋይሎች ለሁሉም የሚታደሉ መሆናቸውንና ከፊሉ በቀኝ እጅ ሌላው በግራውና ከበስተጀርባው የሚሰጠው መሆኑን ማመንንም ያጠቃልላል። ነቢያችን ሙሐመድ (ሰዐወ) በትንሳኤው ቀን ልዩ ውሃ(ሐውድ) ለምዕመናን የሚያጠጡ መሆናቸውን :ገነትና ገሐነም መኖራቸውን :ምዕመናን ጌታቸውን(ሱወ) የሚመለከትና የሚያናግራቸው መሆኑንና በዚህ ርዕስ ሥር የሚጠቃለሉ በቁርአንና በነቢዩ(ሰዐወ) ሐዲስ በተረጋገጡ ሌሎች ጎዳዮች ሁሉ ማመን የዚህ የእምነት መሠረት አካል ነው። በነዚህ ጉዳዮች ሁሉ ማመን አላህና መልከተኛው(ሰዐወ) በገለጹት መልክ ትክክለኛ መሆናቸውን ተቀብሎ ማረጋገጥ ግዴታ ነው።

በ ቀደር" ማመን ደግሞ በአራት ጉዳዮች ማመንን ያካትታል። እነሱም አንደኛ አላህ(ሱወ) የሆነውንና ወደፊት የሚሆነውን ሁሉ በፍጹምነት የሚያውቅ: የባሮቹን ሁኔታዎች ሙሉ በሙሉ የሚያውቅ: ሲሳያቸውን ዕድሜያቸው ሥራዎቻቸውና ሌሎችም ጉዳዮቻቸው ከርሱ በፍጹም የማይሰወሩ :በርሱ ዕውቀት ሥር ያሉ መሆናቸውን ማረጋገጥን ያካትታል። አላህ(ሱወ) እንዲህ ብሏል:-

﴿إن الله بكل شيء عليم﴾.

*..አላህ በነገሩ ሁሉ ዐዋቂ ነውና።"34*

---

34.አል-ተውባህ(9):115

وقال عز وجلّ : ﴿لتعلموا أن الله على كل شيء قدير وأن الله قد أحاط بكل شيء علمًا﴾ .

*..አላህ በነገሩ ሁሉ ላይ ቻይ መኾኑን: አላህም በነገሩ ሁሉ በዕውቀት ያካበበ መሆኑን ታውቁ ዘንድ(ይህንን አሳወቃችሁ)።"35*

ሁለተኛው ነጥብ ደግሞ አላህ(ሱወ) የወሰናቸውንና የፈረዳቸውን ነገሮች ሁሉ የመዘገበው መሆኑን ማወቅ ነው። አላህ(ሱወ) እንዲህ ብሏል:-

﴿قد علمنا ما تنقص الأرض منهم وعندنا كتاب حفيظ﴾ .

﴿وكلّ شيء أحصيناه في إمام مبين﴾ .

﴿ألم تعلم أن الله يعلم ما في السماء والأرض إن ذلك في كتاب إن ذلك على الله يسير﴾ .

*"ከነሱ (አካል) ምድር የምታጎድለውን: በእርግጥ አውቀናል: እኛም ዘንድ ጠባቂ መጽሐፍ አለለ።"36*

*"..ነገሩንም ሁሉ: ገላጭ መሪ በኾነ መጽሐፍ ውስጥ አጠቃለልነው።"37*

*"አላህ በሰማይና በምድር ውስጥ ያለን ሁሉ በእርግጥ የሚያውቅ መኾኑን አታውቅምን? ይህ በመጽሐፍ ውስጥ(የተመዘገበ) ነው: ይህ በአላህ ላይ ገር ነው።"38*

---

35.አል-ጠላቅ(65):12

36.ቃፍ(50):4

37.ያሲን(36):12

38.አል-ሐጅ(22):70

ሶስተኛው ጉዳይ ደግሞ ፍጹም የሆነ ተፈጻሚነት ባለው የአላህ ፈቃድ በማመን እርሱ የፈቀደው ይሆናል እርሱ ያልፈቀደው ነገር በፍጹም የማይሆን መሆኑን ማወቅ ነው። አላህ(ሱወ) እንዲህ ብሏልና:-

﴿إن الله يفعل ما يشاء﴾ .

﴿إنما أمره إذا أراد شيئًا أن يقول له كن فيكون﴾ .

﴿وما تشاؤن إلاّ أن يشاء الله ربّ العالمين﴾ .

*..አላህ የሻውን ይሰራልና።"39*

*ነገሩም አንዳችን በሻ ጊዜ ኹን ማለት ነው፡ ወዲያው ይኾናልም።"40*

*የዓለማት ጌታ አላህ ካልሻም አትሹም።"41*

አራተኛው ነጥብ አላህ(ሱወ) የፍጥረታት ሁሉ ፈጣሪ ጌታ መሆኑንና ከርሱ በስተቀር ሌላ ፈጣሪ ጌታ አለመኖሩ ማወቅ ነው። አላህ(ሱወ) እንዲህ ብሏል:-

﴿الله خالق كل شيء وهو على كل شيء وكيل﴾ .

*አላህ የነገሩ ሁሉ ፈጣሪ ነው። እርሱም በነገሩ ሁሉ ላይ አስተናባሪ ነው።"42*

---

39.አል-ሐጅ(22):18

40.ያሲን(36):82

41.አል-ተክዊር(81):29

42.አል-ዙመር(39):62

﴿يا أيها الناس اذكروا نعمة الله عليكم هل من خالق غير الله يرزقكم من السماء والأرض لا إله إلاّ هو فأنّى تؤفكون﴾.

*"እላንተ ሰዎች ሆይ! በናንተ ላይ(ያለውን) የአላህን ጸጋ አስታውሱ፤ ከአላህ ሌላ ፈጣሪ አልለን? ከሰማይና ከምድርም ሲሳይን የሚሰጣችሁ አልለን? ከርሱ በስተቀር አምላክ(ሰጪም) የለም፤ ታዲያ ወዴት ትዞራላችሁ።"43*

በ ቀድር" ማመን በነዚህ ከላይ በተጠቀሱት አራት ጉዳዮች ማመን ያጠቃልላል። ከነዚህ ጉዳዮች ከፊሉን ከሚያስተባብሉት የከላሽ ቡድኖች (አህሉል ብደዕ) በተቃራኒ፤ የሱንና ወገኖች ዘንድ በቀደር ማመን በአራቱ ነጥቦች ማመንን ያካትታል።

ኢማን(እምነት) ከቃልና ከተግባር የተገነባ አላህ ያዘዛቸውን ነገሮች (ጧዓት) በመሥራት የሚጨምርና የሚፋፋ፤ የአላህን ትዕዛዛት በመጣስም የሚቀንስና የሚቀጭጭ መሆኑን፤ እንደ ዝሙት፤ ሥርቆት ፤አራጣ አስካሪ መጠጥ መውሰድ ፡ወላጆችን ማስቀየምና ሌሎች ታላላቅ ኃጢአቶችን መፈጸም ብቻ ፤ከሙስሊሞች መካከል በአላህ ያላጋራ(ያላሻረከ) ፤አላህን ያስተባበለና አላህ የከለከላቸውን ነገሮች ይፈቀዳሉ ብሎ ያመነ ካልሆነ በስተቀር አንድን ሙስሊም ከሓዲ (ካፊር) ነው ማለት የማይፈቀድ መሆኑንም አውቆ ማመን በአላህ ከማመን ጋር የሚደመር ነው። አላህ(ሱወ) እንዲህ ብሏልና:-

﴿إن الله لا يغفر أن يشرك به ويغفر ما دون ذلك لمن يشاء﴾

*አላህ በርሱ ማጋራትን በፍጹም አይምርም፡ ከዚህ ሌላ ያለውንም (ኃጢአት) ለሚሻው ሰው ይምራል።..'44*

---

43.ፋጢር(35):3

44.አል-ኒሳእ(4):48

ከአላህ መልክተኛ(ሰዐወ) ሐዲስ በተረጋገጠ መሠረት የሰናፍጭ ፍሬ ያህል እንኳ ልቡ ውስጥ እምነት ያለውን ሰው አላህ ከገሐነም እሳት ያወጠዋል። ለአላህ ብሎ ሌላውን ሰው መውደድና ለርሱም ብሎ መጥላት፣ ወዳጅነትንና ጠላትነትንም አላህን ከመውደድና አላህን ከመታዘዝ (ከመውደድ) አንጻር ማየት በአላህ ከማመን ሥር ይካተታል። በዚህ መሠረትም አንድ አማኝ(ሙእሚን) አማኞችን ይወዳል ከሓዲዎችን ይጠላል። ከሕዝበ እስላሙ የምዕመናን ሁሉ ግንባር ቀደም የአላህ መልክተኛ (ሰዐወ) ባልደረቦች(ሰሓባ) ናቸው። በመሆኑም ብዙኃኑ የሱን'ና ወገኖች(አህሉ-ሱን'ና) የነቢዩን ሰሃቦች ይወዳሉ፤ ይደግፋሉ። ከነቢያት ቀጥሎ ከመላው የሰው ልጅ የሚበልጡ መሆናቸውንም አምነው ይቀበላሉ። የአላህ መልክተኛ (ሰዐወ) እንዲህ ብለዋልና:-

«خير القرون قرني

ثم الذين يلونهم ثم الذين يلونهم» متفق على صحته .

*"ከትውልዶች ሁሉ በላጩ የኔ (በከፍለ ዘመኔ የኖረ) ትውልድ ነው። ከዚያም ቀጥሎ ያለው ትውልድ ከዚያም (በሶስተኛ ደረጃ የኖረ) ትውልድ ነው።"45*

ከሰሓቦቹ መካከል ደግሞ በላጮቹ በቅደም ተከተል አቡበክር፣ ዑመር፣ ዑስማንና ዓሊይ መሆናቸውን ያምናሉ። ከአራቱ ቀጥሎ በነቢዩ(ሰዐወ) አንደበት የገነት መሆናቸው የተመሰከረላቸው አሥሩ ሰሓቦች ናቸው ብለው ይቀበላሉ። በሰሓቦቹ ዘመን በመካከላቸው ተከስተው የነበሩት አለመግባባቶች ላይ ከመተቸትም ይቆጠባሉ።

---

45. ቡኻሪና ሙስሊም የዘገቡት ሐዲስ

በነዚያ ጉዳዮች ላይ ሰሓቦች ወስደውት የነበረው የተለያየ አቋም፡ ግልጽ የቁርአንና የሐዲስ አንቀጾች በሌላቸው ጉዳዮች ላይ ግንዛቤያዊ ጥረት(እጅትሃድ) አድርጎ ንጽጽሮሻዊ የሕግ አቋም ማመንጨትን ከሚፈቅደው እስላማዊ መርህ ላይ የተመረኮዘ እንደነበረም አህሉ-ሱን'ና ያምናሉ። በዚህም አላህ ዘንድ ተወዳጅነት ያለው አቋም መያዝ የቻለ ሰው አላህ ዘንድ ድርብ ምንዳ እንዳለውና የተሳሳተ አቋም የያዘ ደግሞ አንድ ምንዳ የሚያገኝ መሆኑንም አምነው ይቀበላሉ። ከነቢዩ (ሰዐወ) ቤተሰቦችና ዘመዶች በነቢዩ ያመኑትን ይወዳጃሉ። የነቢዩን ባለቤቶችም እመምእመናን መሆናቸውን በመረዳት ሁሉንም ይወዳሉ ያከብራሉ። የአላህን ውዴታም ይመኙላቸዋል። የአላህ መልክተኛ (ሰዐወ) ሰሓቦችን ከሚጠሉ ከሚሳደቡና ለነቢዩ ቤተሰቦች ያላቸውን ታማኝነትና ወዳጅነት ከሚገባው በላይ ከሚያከብሩ አላህ(ሱወ) ከሰጣቸው ደረጃ በላይ ከሚሰጧቸው አምቢተኞችም ሱኒዎች ራሳቸውን ንጹሕ ያደርጋሉ። የነቢዩን(ሰዐወ) ቤተሰቦች በቃልም ይሁን በተግባር ከሚያውኩና ከሚያስቸግሩ ጠሮቻቸውም እንደዚሁ ራሳቸውን ያርቃሉ።

በዚህ አጠር ያለ ንግግር ውስጥ ያወሳናቸው ነገሮች ሁሉ አላህ መልክተኛውን (ሰዐወ) ከላከበት ትክክለኛ እምነት (ዐቂዳ) ውስጥ የሚጠቃለሉ ናቸው። አላህ ዘንድ ተቀባይነት ያለው መድህን የሚያገኘው ጭፍራ (አልፍርቀቱ-ናጂያ)የሚከተለው የሱን'ና ወገኖች ዐቂዳም ይኸው ነው። ይህን የመድህን ጭፍራ አስመልክተው የአላህ መልክተኛ(ሰዐወ) እንዲህ ብለዋል:-

«لا تزال طائفة من أمتي على الحق منصورة لا يضرهم من خذلهم حتى يأتي أمر الله سبحانه». «افترقت اليهود على إحدى وسبعين فرقة وافترقت النصارى على اثنتين وسبعين فرقة، وستفترق هذه الأمة على ثلاث وسبعين فرقة كلها في النار إلاّ واحدة فقال الصحابة: من هي يا رسول الله؟ قال: من كان على مثل ما أنا عليه وأصحابي»

*"የአላህ(ሱወ) ውሳኔ እስከመጣ ድረስ ከሕዝቤ ውስጥ አንዱ ጭፍራ በሐቅ ላይ ጸንቶ ያልደገፉቸው ሰው ሳይጎዳቸው የተረዱ (የታገዙ) እንደሆኑ ይቆያሉ።"*

*"የአይሁድ ሕዝብ ሰባ አንድ ቦታ ተከፋፍለዋል። ክርስትያናች ደግሞ በሰባ ሁለት ቡድን ተከፋፍለዋል። ይህ ሕዝብ (ሕዝበ እስላም) ደግሞ ሰባ ሶስት ቡድን ይከፋፈላል። ከዚህ ውስጥ አንድ ቡድን ብቻ ሲቀር ሁሉም የእሳት ናቸው።"የአላህ መልክተኛ ሆይ! ይህች ቡድን የትኛዋ ነች" በማለት ሶሓቦች ሲጠይቁ:-*

*"እኔና ባልደረቦቼ (ሶሓቦቼ) ያለንበትን በመሰለ መንገድ ላይ የሆነ ሰው ነው።" በማለት መለሱ።*

ይህም መከተሉ ግዴታ የሆነ በጽናት ቀጥ ተብሎ ሊያዝ የሚገባውና ከተቃራኒው በትጋት ሊጠነቀቁ የሚያስፈልግ እምነት (ዐቂዳ) ነው።

ከዚህ እምነት የተዛነፉና በተጻራሪው መንገድ የሚጓዙ ወገኖች በብዙ ክፍል ይፈረጃሉ። የጣኦታት የቁሳቁስ የመላእኮች የጻድቃን የአጋኜን የዛፍና የድንጋይ ወዘተ አምላኪዎች ይገኙባቸዋል። እነኝህ ክፍሎች ለአላህ ነቢያት ጥሪ ምላሽ ያልሰጡት ጥሪውን የተጻረሩና የቁረይሾችና ሌሎች የዐረብ ጎሳዎች በነቢያችን በሙሐመድ (ሰዐወ) ላይ እንዳደረጉት ሁሉ ከጥሪው ፊት በጠላትነት የተጋረጡ ክፍሎች ናቸው። ጉዳዮቻቸውን እንዲፈጽሙላቸው በሽተኞቻቸውን እንዲፈውሱላቸው በጠላቶቻቸው ላይ ድል እንዲሰጧቸው ጣኦቶቻቸውን ይማጸኑ ነበር። ለጣኦታቱ ያርዱና ይሳሉም ነበር። የአላህ መልክተኛ(ሰዐወ) ይህን ድርጊታቸውን በመቃወም ሲያጥ ላሉባቸውና አላህን ብቻ በፍጹምነት እንዲገዙት ሲያዟቸው በመገረምና በእምቢታ እንዲህ አሏቸው:-

﴿أجعل الآلهة إلهاً واحدًا إن هذا لشيء عجاب﴾.

*“አማልክቶቹን አንድ አምላክ አደረጋቸውን? ይህ አስደናቂ ነገር ነው፤(አሉ)።”46*

ነቢዩ(ሰዐወ) ጣኦታውያኑን ወደ አላህ መጥራቱን፡ ከባዕድ አምልኮ ማስጠንቀቁንና የጥሪያቸውን እውነታ በዝርዝር ማስረዳታቸውን አላህ ከመካከላቸው የሚሻውን ወደ ቅኑ መንገድ እስኪመልሳቸው ድረስ በትጋት ቀጠሉ። ከዚያም በኋላ ቡድን በቡድን እየሆኑ በብዛት ወደ አላህ ሃይማኖት መግባት ጀመሩ። በዚህም የአላህ ሃይማኖት የአላህ መልክተኛ(ሰዐወ) ባልደረቦቻቸውና አርአያቸውን በቅንነት የተከተሉ ተከታይ ትውልዶች ባደረጉት ያላቋረጠና ረዥም ትግልን በጠየቀ ጥሪ (ደዕዋ) ሃይማኖቱ ከሁሉም ሃይማኖቶች በላይ ሆኖ ወጣ። ከጊዜ በኋላ ግን ሁኔታዎች ተለዋወጡና ብዙኃኑ ሕዝብ ላይ ማይምነት አይሎ ነቢዮችና ጻድቃንን ከሚገባው ቦታ በላይ እየሰጡ ማምለክ፣በነሱ መማለድና የመሳሰሉ የማጋራት(የሽርክ) ዓይነቶች ውስጥ በመዘፈቅ ወደ ጥንቱ የዘመነ ማይምነት እምነት አብዛኛው ሕዝብ ተመለሰ። የ“ላኢላሀ ኢላሏሀ” ትርጉምን የዐረብ ከሐዲዎች (ካፊሮች) በተረዱት መንገድ ማወቅ ተሳናቸው።

ይህ የማጋራት (የሽርክ) ሁኔታ ማይምነት በማየሉና ዘመኑ ከዘመነ ነቢይነት (ዐስሩ-ኑቡዋ) በመራቁ ምክንያት እስካሁኑ ዘመናችን ድረስም በሰዎች መካከል መስፋፋቱን ቀጥሏል።

የኋለኞቹ ዘመን አጋሪዎች (ሙሽሪኮች) ጥርጣሬና ማመካኛ ነጥብ ያው የጥንቶቹ ጥርጣሬና ውዥንብር(ሹብሃ) ነው። ቀጥሎ በሰፈረው የአላህ ቃል አማካይነት ተገልጾ የነበረው:-

﴿هؤلاء شفعاؤنا عند الله﴾.

---

46.ሷድ(38):5

﴿ما نعبدهم إلاّ ليقربونا إلى الله زلفى﴾

*“..እነዚህም አላህ ዘንድ አማላጆቻችን ናቸው ይላሉ:..”47*

*“..(ጣኦታትን) ረዳቶች የያዙት፣ ወደ አላህ ማቃረብን እንዲያቃርቡን እንጂ ለሌላ አንግገዛቸውም: (ይላሉ)፣..”48*

አላህ(ሱወ) ይህን ውዥንብር ውድቅ አድርጎባቸው የፈለገውን ዓይነት ፍጡር ከአላህ ሌላ አምላክ አድርጎ ያመለከ ሰው በአላህ ያጋራና አላህን የካደ መሆኑን በማረጋገጥ እንዲህ ብሏል:-

﴿ويعبدون من دون الله مالا يضرهم ولا ينفعهم
ويقولون هؤلاء شفعاؤنا عند الله﴾.

﴿قل أتنبؤن الله بما لا يعلم في السموات ولا في الأرض
سبحانه وتعالى عما يشركون﴾.

*“ ከአላህም ሌላ የማይጎዳቸውን የማይጠቅማቸውንም፣ ይግገዛሉ: እነዚህም አላህ ዘንድ አማላጆቻችን ናቸው ይላሉ:..”49።*

ይህን አባባላቸውንም አላህ(ሱወ) እንዲህ በማለት መልሶላቸዋል:-

*“..አላህን በሰማያትና በምድር ውስጥ የማያውቀው ነገር ኖሮ ትነግሩታላችሁን? በላቸው: ከሚያጋሩት ሁሉ ጠራ: ላቀም።”50*

---

47.ዩኑስ(10):18

48.አል-ዙመር(39):3

49.ዩኑስ(10:18

50. ዩኑስ(10)18

በዚህ አንቀጽ ውስጥም ከርሱ በስተቀር ነቢያትንም ሆነ ጻድቃንን ማምለክ ትልቁ ማጋራት (አሽ-ሽርኩል አከበር) መሆኑን አላህ(ሱወ) ገልጿል። አላህ(ሱወ) እንዲህ ብሏል:-

﴿والذين اتخذوا من دونه أولياء ما نعبدهم
إلّا ليقربنا إلى الله زلفى﴾.

*"..እነዚያም ከርሱ ሌላ (ጣኦታትን) ረዳቶች የያዙት: ወደ አላህ ማቃረብን እንዲያቃርቡን እንጂ ለሌላ አንገገዛቸውም: (ይላሉ):..."51*

አላህ(ሱወ) ለዚህ መልስ ሲሰጣቸው እንዲህ ብሏቸዋል:-

﴿إن الله يحكم بينهم فيما هم فيه يختلفون إن الله لا يهدي من
هو كاذب كفار﴾.

*"..አላህ በዚያ እነርሱ በርሱ በሚለያዩበት ነገር በመካከላቸው ይፈርዳል: አላህ እርሱ ውሸታም ከሓዲ የሆነን ሰው አያቀናም።"52*

በዚህም ከርሱ በስተቀር ሌላን በመማጸን በመፍራት በመከጀልና በመሳሰሉት የአምልኮ መልኮች መግገዛታቸው ክህደት(ኩፍር) መሆኑን ግልጽ አድርጎላቸው ጣኦቶቻቸው ወደርሱ የሚያቀርቧቸው አማላጆች ናቸው የሚለውን አባባላቸውን አስተባብሎባቸዋል።

ክህደት(ኩፍር) ከሆኑትና ትክክለኛውን እምነት(ዐቂዳ) የሚጻረሩና የአላህ ነቢያት(ዐሰወ) ይዘው ከመጡት እምነት ጋር የማይጣጣሙ ከሆኑት ውድቅ እምነቶች መካከል፣ በዘመናችን የማርክስና የሌኒን ተከታዮች የሆኑና ሌሎችም የኢአማኝነት (Etheism) ደቀመዛሙርት የሚሰብኩት እምነት አንዱ ነው።

---

51 . አል-ዙመር(39):3

52.አል-ዙመር(39)3

ኢአማኒነት ሶሻሊዝም ኮሙኒዝም ወይም በዕሲዝም ተብሎ ቢጠራ ወይም በሌሎች ስሞች ቢሰየም: ከነዚህ ክፍሎች አበይት መሠረቶች አንዱ አምላክ የለም ሕይወት ቁስአካል ነች የሚል ከመሆኑም በላይ ዳግም ሕይወትን ገነትና ገሐነምን የሚያስተባብሉ ሁሉም ዓይነት ሃይማኖቶችን የሚክዱ በመሆናቸው ሁሉም የክህደት (የኩፍር) መንገዶች ናቸው። መጻሕፍቶቻቸውን ያየና አቋማቸውን ያጠና ሰው ይህንኑ በግልጽና በተጨባጭ ማወቅ ይችላል። ይህ እምነት መለኮታዊ ሃይማኖቶችን በጥቅሉ የሚጻረር እንደመሆኑ መጠን ተከታዮቹን በዛሬው ዓለማዊ ሕይወትም ሆነ በወዲያኛው ለከፋ መጨረሻ የሚያስት ለመሆኑ ጥርጥር የለውም።

እውነትን ከሚጻረሩት እምነቶች መካከል አንዳንድ ሚስጥራውያን (ባጥንያ እና ከፊል ሱፊዎች) ጻድቃን ብለው የሚጠሯቸው አንዳንድ ሰዎች የፍጥረታት ጉዳዮችን በማቀናበር ረገድ ከአላህ ጋር ይጋራሉ በማለት ጣኦቶቻቸውን ከራሳቸው በፈጠሯቸው ስሞች የሚሰይሙበት(ቁጥብ ገውስ ወዘተ) ሁኔታ አንዱ ነው። ይህ ዓይነቱ በአላህ ጌትነት ላይ ከሚፈጸሙ የማጋራት(የሽርክ) ዓይነቶች ሁሉ የከፋው ነው። ከዘመነ ማይምነት ዐረቦች ሽርክም የከፋ ነው። የዐረብ ጣኦታውያን በአምልኮት እንጂ በጌትነቱና በኃያል አድራጊነቱ በአላህ አያጋሩም ነበርና። ባዕድ አምላክ የሚግገዙ በደስታ ጊዜ ነበር። በጭንቀት ጊዜ ግን አምልኮታቸውን ለአንድ አላህ ብቻ ፍጹም ያደርጉ ነበር። ይህንኑ በማስመልከት አላህ(ሱወ) እንዲህ ብሏል:-

﴿فإذا ركبوا في الفلك دعوا الله مخلصين له الدين فلمّا نجاهم إلى البر إذا هم يشركون﴾.

*በመርከቦች ውስጥ በተሳፈሩ ጊዜም: አላህን: መግገዛት ለርሱ ብቻ ያጠሩ ኾነው ይጠሩታል: ወደ የብስ (በማውጣት) ባዳናቸው ጊዜም ወዲያውኑ እነርሱ(ጣኦታትን) ያጋራሉ።"53*

---

53.አል-ዐንከቡት(29):65

ፈጣሪ ጌትነት የአላህ ብቻ መሆኑን ግን ያረጋግጡ እንደነበር ከሚከተለው አንቀጽ ማረጋገጥ ይቻላል:-

﴿ولئن سألتهم من خلقهم ليقولن الله﴾.

﴿قل من يرزقكم من السماء والأرض أم من يملك السمع والأبصار ومن يخرج الحي من الميت ويخرج الميت من الحي ومن يدبّر الأمر فسيقولون الله فقل أفلا تتقون﴾.

*" ማን እንደፈጠራቸውም ብትጠይቃቸው: በእርግጥ አላህ ነው: ይላሉ።.. "54*

*"ከሰማይና ከምድር ሲሳይን የሚሰጣችሁ ማን ነው? መስሚያዎችንና ማያዎችንስ የፈጠረ ማን ነው? ከሙትም ሕያውን: የሚያወጣ ከሕያውም ሙትን: የሚያወጣስ ማን ነው? ነገሩን ሁሉ የሚያስተናብርስ ማን ነው? በላቸው፤ አላህ ነው፤ ይሉሃል፤ ታዲያ (ለምን ታጋሩላችሁ?) አትፈሩትምን? በላቸው።"55*

ይህ አይነት ይዘት ያላቸ ቁርአናዊ አንቀጾች በጣም ብዙ ናቸው።

የኋለኛው ዘመን አጋሪዎች ከጥንቶቹ ጣኦታውያን ላይ በሁለት በኩል ጭማሪ ይዘው ቀርበዋል። አንደኛው:- አንዳንዶቻቸው በአላህ ጌትነትና አስተናባሪነት ሌሎች ፍጡራንን በማጋራት በኩል ነው። ሁለተኛው ደግሞ በደስታም ሆነ በጭንቀት ጊዜ የሚያጋሩ መሆናቸው ነው። ይህንን ከነርሱ ጋር አብሮ የኖረና በጥልቀት የሚያውቃቸው ሰው በሚገባ ያውቃል። በምድረ ግብጽ በሑሰይንና በበደዊ መቃብሮች አጠገብ፤ በኤደን በዐይደሩስ መቃብር፤ በየመን በአልሓዲ መካነ መቃብር፤ በሶርያ በእብኑ ዐረቢ መቃብር፤ በኢራቅ በሸይኽ ዐብዱልቃድር ጂይላኒ መካነ መቃብር ዙሪያና በሌሎቹም ታዋቂ መካነ

---

54. አል-ዙኽሩፍ(43):87

55.ዩኑስ(10):31

መቃብሮች ዘንድ ተራው ሕዝብ ለአላህ ብቻ የሚገቡ የአምልኮት ሁኔታዎችን ለነዚህ ሰዎች በማዞር የአላህን መብት በመጋፋት የሚያሳዩትን ድርጊት ያስተዋለ ሰው ይህን የማጋራት አዝማሚያ በሚገባ ይገነዘባል። ይህን አስከፊ ተግባራቸውን የሚቃወምና አላህ ነቢዩ ሙሐመድንና ከርሳቸው የቀደሙትን ነቢያት የላከበትን የተውሒድ እውነታ የሚያብራራላቸው ሰው ጥቂት መሆኑ በጣም አሳዛኝ ነው!! አላህ (ሱወ) እነዚህን ወገኖች ወደ ትክክለኛው ጐዳና እንዲመልሳቸው፡ ወደ እውነት ጥሪ የሚያደርጉ መምህራን በመካከ ላቸው እንዲበዙ እንድያደርግ ፡ሙስሊም መሪዎችና ዓሊሞች ይህን የማጋራት (የሽርክ)አዝማሚያና መንሥኤውን ለመዋጋትና ለማስወገድ እንዲያስችላቸው እንለምነዋለን። እርሱ ሰሚውና ቅርብ ነውና።

የአላህን ስሞችና ባህርያት አስመልክቶ ትክክለኛውን እምነት (ዐቂዳ) ከሚጻረሩት እምነቶች መካከል የከላሽ(ብድዓ) ቡድኖች እንደነ ጀህሚያ ሙዕተዝላና የነሱን ፈር የተከተሉ ቡድኖች ይገኛሉ። እነዚህ ቡድኖች የአላህን (ሱወ) ባሕርያት ያስተባብላሉ። ሙሉእ ባህርያቱን ትርጉም አልባ ባዶ ቃላት በማድረግ በቁሳቁስ ግዑዝ አካላትና ሊሆኑ በማይችሉ ባህርያት ይገልጹታል። አላህ ግን ከሚሉት ሁሉ ፍጹም የጠራና የላቀ ጌታ ነው። በዚህ ፍረጃ ውስጥ እንደ አሻዕራ ያሉ ከፊሉን ባህርያት አረጋግጠው ከፊሉን የሚያስተባብሉ ክፍሎችም ይካተታሉ። አሻዕራዎች ከፊሉን ባህርያት እንዳረጋገጡ ሁሉ ማስረጃዎቹን ከመቃረን ወጥተውና ራሳቸውን በራሳቸው ከመቃረንም ተላቀው ያስተባበሉትንም የአላህ ባህርያት መቀበል ይኖርባቸዋል። አህሉ-ሱን'ና ግን አላህ ለራሱ ያረጋገጠውን ወይም ነቢዩ (ሰዐወ) ያረጋገጡለት ስሞችና ባህርያቱን በሙሉእነት መልኩ በማረጋገጥ፡ ከፍጡራኑ ጋር በምንም መንገድ የማይመሳሰልና የማይነጻጸር አድርገው እርሱን በማጥራት፡ ባህርያቱን ትርጉም የለሽ ባዶ ቃል በማያድርግ ሁኔታ በማረጋገጥ ማስረጃዎቹን ሙሉ በሙሉ ተግባራዊ ያደርጋሉ። በዚህም ከማዛባትና ትርጉም አልባ ከማድረግ ጉድለት ተጠብቀው ሌሎች ከወደቁበት ራስን በራስ ከመቃረን ነፃ ናቸው። ይህም በዛሬው ምድራዊ ዓለምም ሆነ በነገው ዘለዓለማዊ ዓለም ሕይወት ለድልና ለመድህን የሚያበቃ መንገድ ነው።

የሕዝበ እስላሙ ቀደምት ደጋግ አበውና መሪ ሊቃውንት የተከተሉት ቀጥተኛው መንገድም ይኸው ነው። የመጀመሪያዎቹ መድህን መንገድም ለመጨረሻዎቹም ብቸኛው የመድህን መንገድ ነው። እሱም ቁርአንና ሐዲስ በመከተል ሁለቱን የሚቃረን እርግፍ አድርጎ መተው ነው።